# ኢትኦጵ

ቅፅ 5 ቁጥር 059 ሰኔ 1996 ዓ.ም.



"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የወንበዴዎች መሰብሰቢያ ከሆነች ሰነበተች"

እነ አቡነ መልከፀዴቅ (ከአሜሪካ)

"ሌቦችና ቀማኞች ሐገራቸውን የከዱት ናቸው"

እነ አቡነ ጳውሎስ (ከአዲስ አበባ)

## "እነ ዶክተር ገብረአብ በዘር ማጥፋት መጠየቅ አለባቸው"



የጠፉት የጋምቤላ ፕሬዘዳንት
አኬሎ አኳይ
ከኢትኦጵ
ጋር ያደረጉት ቃለ ምልልስ

## ስለመጪው ምርጫ ከመኢሶን የቀረበ የውይይት መንደርደሪያ ሰነድ

"የቀረበብኝን ክስ እንኳንስ ሕይወቴ አፅምና መቃብሬ አይቀበሉትም"

ሻለቃ ካሳዬ አራጋው

## አባቴ ከቡር ሞያውን በውስጤ ዘርቷል

አርቲስት ቴዎድሮስ ተሰፋዬ







...ዛሬ የሚያሳስበውና የሚያስፈራው ጠ/ሚኒስትርነቱና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱ በትግራይ ተወላጆች እጅ በርስትነት እንዲቀጥል መደረጉ፣ ፀጥታውን፣ መከላከያውን፣ የፖሊስ ሠራዊቱን በዋናነት እነርሱ ብቻ በኋ[illegible]ነት እንዲመሩት መወሰ[illegible] ሳይሆን ይኸው ሁኔታ [illegible]ልጥ እየተጠናከረ መምጣቱ ነው። [illegible].አሁን ባለው የካቢኔ ድል

# ድብቁ...

(ከገፅ 4 የዞረ)

ላይ እንደሚጥሉ የሚያወሱ ታሪኮችን ሁላችንም እንሰማለን:: ማንም ይሁን፣ ምን ያህልም ስኬታማ ይሁን፣ እያንዳንዱ ወንድ አካላዊ ተፈላጊነትን ይሻል:: አንቺ ሁልጊዜ ፈቃደኛ አለመሆን ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ ለወሲብ ልታነሳሸውና ልታነቃቂው ይገባል:: ታዋቂው የፊልም አክተር ፖል ኒውማን አንድ ግዜ «እቤቴ ስቴክ እያለልኝ ከጋብቻ ውጭ ሄጄ ሃምበርገር መፈለግ አይኖርብኝም» ማለቱ ይታወሳል::

እርግጥ ነው ሌላም አማራጭ አለ:: የአንቺን ጥልቅ ስሜት ወይም የሚገፋ ስሜት የሚጠብቀው ከሌለ ለወሲብ ምላሽ ለመስጠት አስቸጋሪ ይሆናል:: የእኔ ኮርስ ለወንዶች «ሴት ልጅ ለአንተ ፍላጐት ምላሽ እንድትሰጥህ ከፈለግህ ደግነትን፣ ጨዋነትን፣ ታማኝነትን፣ ፍላጐትን፣ እንክብካቤን፣ ትዕግስትንና ትኩረትን ሳትቆጥብ ስጣት» በማለት ይመክራል:: በመሆኑም ልዩ፣ የምትፈልግና የምትደነቅ መሆኗ የሚነገራት ሴት ከተተወችውና ከተዘጋጀችው ሴት ይልቅ ለወሲባዊ ተራክቦ ዝግጁ ናት::

### አይንህ አያርፍም በሚል እንጨቃጨቃለን

<u>ውድ ዶክተር ኤለን</u>:- እኔና ባለቤቴ ከተጋባን ገና አንደ ዓመታችን ሲሆን፣ ሁልግዜም በተመሳሳይ ጉዳይ እንጨቃጨቃለን:: ባለቤቴ በማጋዚናች ላይ ያሉ ዕርቃን ሴቶችን ፎቶ ሳይም ሆነ አብረን ወጥተን አይኔን ሌላ ሴት ላይ ጣል ሳደርግ በጣም ትበሳጫለች፤ ብዙ ወንዶች ይህን እንደሚያደርጉና ምንም ከፋት እንደሌለው አንቺም የምታምኚበት ይመስለኛል:: ታዲያ እኔ ጤናማና ትክክለኛ ሰው መሆኔን እንዲት አሳምኜ እንዳትበሳጭ ማድረግ እችላለሁ?

*ዴቪድ*

<u>ውድ ዴቪድ</u>:- ትክክል ነህ:: ብዙ ወንዶች ቆንጆ ሴትን በማየትና ከማጋዚን ላይ ራቁት ሴቶችን በመመልከት ይደሰታሉ:: ይህ እንዳለ ሆኖ ታዲያ ወንድ ልጅ አንዴ በፍቅር ወድቆ ትዳር ከመሠረተ በኋላ ከራሱ በላይ የሚያስባቸው ነገሮች ይኖራሉ:: የእኔ የእውነተኛ ፍቅር ትርጉም «የሌላ ሰው ደስታና ደህንነት ልክ የራስህን ያህል አስፈላጊ ሲሆን» ነው:: ባለቤትህ የአንተ ባሕሪ እሷን እንደማያስደስታት እየነገረችህ አንተ የእሷ ስሜት ስሕተት መሆኑን ነገሬ እንዳሳምንልህ እኔን ትጠይቀኛለህ:: ይህንማ ማድረግ አልችልም:: እውነቱን ልንገርህና አንተ በዚህ ባሕሪ የምትቀጥል ከሆነ ባለቤትህ ቁጡ፣ ቀዝቀዛና መራር ሴት እየሆነች ትመጣለች:: የበሰለና አፍቃሪ ሰው ለትዳሩ ሲል የተወሰኑ ነገሮችን መስዋዕት ማድረግ ይኖርበታል:: ልጆች ሲጨመሩ ደግሞ አሁንም ተጨማሪ መስዋዕትነት ይኖራል:: እንበልና እስከ ሌሊቱ 10 ሰአት ፓርቲ ማምሸት ብትፈልጉ ልጃችሁ በጥዋት ነቅቶ ትምሕርት ቤት መሄድ አለበትና አታደርጉትም::

የዕርቃን ሴቶችን ምስል መመልከትህና ከእንግዳ ሴቶች ጋር መሽኮርመምህ አጋርህን ይጐዳታል:: ስለሆነም ስሜትህን በቀላሉ ተቆጣጠርና አታድርገው:: በነገራችን ላይ ባለቤትህ አብራህ በማትሆንበት ግዜ ሌላ ሴትን እንዳታይ ሊያደርግህ የሚችል ማንም የለም:: ይሁን እንጂ ለባለቤትህና ለትዳር ካለህ ፍቅርና አክብሮት በሚመነጭ እምነት አብራችሁ ስትሆኑ ትኩረትህ እሷ ብቻ እንድትሆን መማር ይኖርብሃል::

### ባለቤቴ የበለጠ ስሜታዊ ፍቅርን ትሻለች

<u>ውድ ዶክተር ኤለን</u>:- አስደሳች ወይም ስሜታዊ ፍቅር (Romance) ምንድነው? እየሽ ባለቤቴ የበለጠ ስሜታዊ አፍቃሪ እንድሆን በየግዜው ትነግረኛለች:: እኔም ጉዳዩን ሳላጣጥል ልሞክረው ወስንኩና ባለቤቴን «እሺ የምትደኝን ስሜታዊ ፍቅር ንገሪኝና ሳደርገው» ብያት ነበር:: የእሷ መልስ ግን «ስሜታዊ ፍቅር ደሄ፣ ደሄ ነው ካልኩህማ ስሜታዊነቱ ይጠፋል» የሚል ሆነብኝ:: እና እባክሽ እርጂኝ?

*ዳረን*

<u>ውድ ዳረን</u>:- ሁልግዜ ለሴቶች የምነግራቸው ወንዶች የተለየ መንፈስ ያላቸውና የእናንተን አእምሮ የሚያነቡ አይደሉም እያልኩ ነው:: መቼም እርግጠኛ ነኝ የ«ሴቶች ደመነፍስ» ሲባል ሰምተሃል:: በእርግጥም እውነት ነው:: በዚህ ረገድ ሴቶች ተሰጥኦው ያላቸው ሲሆን፣ ወንዶች ግን ይህችን አልታደሏትም:: እናም ሴቷ ምን እንደምትፈልግ እንድትነግራቸው ይሻሉ:: ከልባቸውም ሴትን ልጅ ለወሲብ የሚያነሳሳት ምን እንደሆነ ማወቅ ይፈልጋሉ:: እና ምን ምን አይነት ሮማንቲክ ነገር እንደምትፈልግ የሚጠይቃት ወንድ ያገኘች ሴት ዕድለኛ ናትና መናገር ይገባታል:: አንድ ግዜ ወንዶች ክፍል ውስጥ ሳስተምር «**ROMANCE**» የሚለውን ቃል ጥቁሩ ሰሌዳ ላይ ጻፍኩና ራሳቸውን ሮማንቲክ ነን ብለው ያስቡ እንደሆነ ጠየቅኳቸው:: እናም ብዙዎቹ አልጋ ላይ ጥሩ ናችሁ ወይ እንዳልኳቸው ስለሚያስቡ አዎን አሉኝ:: ይሁን እንጂ ለሴት ልጅ ሮማንስ ግዜን አብሮ ማጥፋት ነው:: ሴቶችን በማስተምርበት ክፍል « **ROMANCE**» የሚለውን ቃል ስፅፍ ሴቶቹ የሚያስቡት፣ አብሮ መደነስን፣ መተቃቀፍን፣ እጅ ለእጅ መያያዝን፣ ረዥም ጉዞ እየሄዱ ማውራትን፣ የሻማ ምሽት ራትን...ወዘተ ነበር:: በሌላ አነጋገር ወንዶች ስሜታዊ ምላሽን ለሴት ለመስጠት ወሲባዊ ርካታን ሲፈልጉ፤ ሴቶች ደግሞ ለወንዶች ወሲባዊ ርካታ ለመስጠት ስሜታዊ ምላሽን ይፈልጋሉ::

ስለዚህ ሮማንስ ውሳኔ ነው:: ሌሎች ሰዎች ያደረጓቸውን በርካታ ምሳሌዎች ትሰማለህ፤ እስከዚያው ባለቤትህን ለሚቀጥለው ቅዳሜ ምሽት እንድትወጡ ቀጠሮ አስያዛት፣ አውጣና ራት ወይም ፊልም ወይም ሁለቱንም ጋብዛት፤ እቤት እንደተመለሳችሁ አንድ ሮማንቲክ ዘፈን አድርግና እንድተደንሱ ጠይቃት:: ከዘያም ገንዳህን ውሃ ሞልተህ ወደዚያው ምራትና ከእግር ጥፍሯ እስከ ጠጉሯ እየዳሰስክ ዘና እንድትል አድርጋት::...ሮማንስ ማለት ይኸው ነው::

# ተቃዋሚዎች...

(ከገፅ 9 የዞረ)

ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ ባይሟሉ እንኳን የምርጫውን ቅስቀሳ ማቆም የለብንም፤ ባለ በሌለ ሃይላችን ተንቀሳቅሰን ህዝባችንን ለማንቀሳቀስ የቆረጥን መሆኑን ከወዲሁ በግልፅና በይፋ ማስቀመጥ ይኖርብናል የሚለው ሃሳብ ተሰንዝሯል:: አንዳንድ ተወካዮች ይህንን አስተሳሰብ የማይጋሩ መሆናቸው በግልፅ ታይቷል:: እነዚህ ወገኖች «እስካሁን ያለው የህብረቱ አስተሳሰብ ሁኔታዎች እንዲሟሉ መደራደር የሚል ነው:: በሌላ በኩል ሁኔታዎች እንዲሟሉ በዲፕሎማሲው መስክ መስራትና እንደ ዚሁም ህዝቡን ማንቀሳቀስ አለብን እንጂ ካሁኑ እንሳተፋለን ማለት የለብንም» በማለት ያላቸውን ልዩነት ገልፀዋል::

እንዲህ አይነቱ አቋም ምርጫው ነፃ ካልሆነ ምንም የረባ ውጤት አያስገኝም ከሚል ስሌት ተነስቶ ወሳኝ የሆነውን የህዝባዊ ማእበል መቀስቀስ ሂደት የሚረሳ አቋም ብቻ አይደለም:: ከሚሰጠው መልስ የሚከተላቸው ጥያቄዎች ይበልጣሉ:: መንግስት መስፈርቶችን መቀበሉ ወይም አለመቀበሉ የሚታወቀው መቼ ነው? ምርጫው ስድስት ወር ሲቀረው? አንድ ወር ሲቀረው? እስኪያሟላ መጠበቃችንን አውቆ ኢ.ህአዴግ ነገሮችን ሆን ብሎ የማጓተት ስትራቴጂ ቢከተልስ? ተሟልቷል፣ አልተሟላም ለማለት ሚኒመም የምንቀበላቸውንና የማንቀባለቸውን ነጥቦች አውጥተናል ወይ? መስፈርቶችን አላሟላም ብለን አኛስ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የጊዜ ገደብ አለን ወይ? መሳተፍ አለመሳተፍ ውሳኔ እስከምንደርስ ባለው ጊዜ ተግባራችን ወይም የትግል አጀንዳችን ምንድን ነው? የህዝባችንን ነፃነትና የዴሞክራሲ ተስፋ በዚህ ውድድር ውጤት ላይ እንተወዋለን ወይስ መስፈርቶች ካልተሟሉ በደፈናው «ምርጫው» ውስጥ አንሳተፍም ከሚለው ሌላ አማራጭና ተጨባጭ የትግል መፈክሮች አሉን? በተሳትፎና በቦይኮት ጉዳይ አሁን ያለው ያልተጣራ ሁኔታ በሙሉ ልብ አጣዳፊ ተግባራትን እንዳንያያዝ አድርጎን ወርቅማ ጊዜ እየባከነ ስለሆነ ህብረቱ በዚህ ጉዳይ ባስቸኳይ ለሁለቱ ጥያቄዎች ግልፅ መልስ መስጠት ይኖርበታል::

አንደኛ:- መስፈርቶች አልተሟሉም ብለን የቦይኮት ውሳኔ ላይ ከደረስን ቦይኮት የምናደርገው ምኑን ነው? አጠቃላዩን የምርጫ ሂደት ነው ወይስ የመጨረሻዋ ቀን የሚካሄደውን የድምፅ መስጠት ሂደት ብቻ? በእኛ ግምት በሁለቱ መካከል ትልቅ ልዩነት አለ:: የሚያዋጣ የሚመስለን አካሄድ መስፈርቶች ተሟሉ፣ አልተሟሉ የምርጫውን ካምፔን በምንም አይነት ቦይኮት አናደርግም ብለን ከተቻለ በአምስት መቶ አርባዎቹ የምርጫ ክልሎች እጩዎች አሰልፈን የኢህአዴግን መንግስት ለመፋለም ባስቸኳይ ዝግጅት መጀመር አለብን የሚል ነው::

ሁለተኛ:- የቦይኮት ውሳኔ ላይ የምንደርሰው መቼ ነው? የቦይኮት ነገር ከመጣ ይህን ምናደርገው በሚልዮን ከሚቆጠሩ ወገኖቻችን ጋር አብረንና በካምፔይኑ ወቅት የተፈፀሙትን ፀረ ነፃ ምርጫ እርምጃዎች በሙሉ በማዕከል ደረጃ መዝግበን በህዝባችንና በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ፊት አጋልጠን እንጂ ከህዝባችን ተነጥለን ብቻችንን መሆን የለበትም:: ይህ ደግሞ ከካምፔይኑ ማብቂያ ላይ ድምፅ ለመስጫው ቀን ሳምንትም ሆነ ሃያ አራት ሰአት ሲቀረን ባጭሩ በመጨረሻዋ ደቂቃ የምንወስነው ነገር መሆን ይኖርበታል:: ከዚህም አልፎ መሄድ ይቻላል:: የምርጫው ሂደት በካምፔይኑ ወቅት ብቻ ሳይሆን የምርጫው እለት በተጨባጭ በሚፈፀሙ ፀረ ነፃ ምርጫና ህገ ወጥ ድርጊቶችና ማጭበርበሮች ሙሉ በሙሉ ሊበከል እንደሚችል ባለፈው የምርጫ ወቅት አይተናል:: በመሆኑም ሕዝባችንን በሚልዮን እንቀሳቅሰን ለቀጣዩ ትግል ተዘጋጅተን እስከተ

ገኘን ድረስ በዋዜማው ከምርጫው ራስን ማግለል እስከ ድምፅ መስጠቱ ሂደትም ድረስ ተሳትፈን፣ በእለቱ የተፈፀሙ ህገ ወጥ ድርጊቶችን አጋልጠን፣ ለውጤቱ እውቅና እንሰጠውም የሚለውን አቋም በምርጫው ማግስት አስተጋብተን እንደ ጆርጂያና ሰርብ ትግላችንን መቀጠል እንችላለን::

በዚህ ነጥብ ስምምነት ላይ ከተደረሰ ስፍር ቁጥር የሌላቸውና እጅግ አጣዳፊ የሆኑት ተግባሮችን ከፊታችን ስለሚደቀኑ በአልሆነ አቅጣጫ በመኳተን በእርግጥ የእኛንና የኢትዮጵያን ህዝብ ወርቃማ ጊዜ እያባከንን እንደሆነ ወዲያውኑ ከፀሃይ ደምቆ ይታየናል:: ከእነዚህ መአት ተግባራት አንፃር ሲታይ አንዱ አጉል ትኩረት የምንለው ለነፃ ምርጫ እኛ ራሳችን ማሟላት ያለብንን ቅድመ ሁኔታዎች «ለጊዜው» ወይም «ወያኔ/ ኢህአዴግ የበኩሉን እስኪያሟላ» በሚል አካሄድ ችላ ብለን ከመንግስት ጋር ለሚደረገው ድርድር እየሰጠን ያለነው ስፍራ ይመስለናል::

### 3. መስፈርቶች እንዲሟሉ ከመደራደር መታገልን እናስቀድም

የነፃ ምርጫ መስፈርቶች ስለሚሟሉበት ሁኔታ ከመንግስት ጋር መደራደር አያስፈልግም አንልም:: የኢህአዴግ መንግስት አለም አቀፋዊ መስፈርቶችን እንዲያሟላ መታገል ያስፈልጋል:: ሆኖም ይህንን በአሁኑ ሁኔታ «በሃገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ መንግስት ከተቃዋሚዎች ጋር ውይይት ከፈተ» በሚለው ነጥብ እንዲውም ከእኛ ይልቅ ኢህአዴግ እየተጠቀመበት ያለውን «ድርድር» ከሚገባው በላይ ተኩረት ሰጥቶ ሌሎች አጣዳፊ ተግባራትን መዘንጋት አያስፈልግም:: ለምን?

አንደኛ፡- ከመንግስት ጋር የሚደረገው ድርድር በዝግ ችሎት መልክ ሳይሆን ህዝቡም እንዲገባበት ለማድረግ መሰረታዊ የሆኑትን ጥያቄዎችን በቀላል ቋንቋና በነጥብ፣ በነጥብ አስቀምጠን ከካምፔይኑም በፊት ሆነ በካምፔይኑ ወቅት የመራጩ ህዝብ መቀስቀሻ መሳሪያ እንድናደርጋቸው ያስፈልጋል:: ይህንን ካደረግን በምርጫው ካምፔይን ወቅት በሚልዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በወያኔ ካድሬዎች በያለበት የሚፈፀሙትን ፀረ ነፃ ምርጫ ድርጊቶች ለመዋጋትና ለማጋለጥ የሚስችላቸው መሳሪያ ሰጠናቸው ማለት ነው:: በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ከኢህአዴግ ጋር ተደራድረን ከምናገኘው ዋስትና ይልቅ በዚህ መልክ የህዝባችን ንቁ ተሳትፎ ሺህ ጊዜ ይበልጥ አስተማማኝ ውጤት ይሰጣል የሚል ፅኑ እምነት አለን::

ሁለተኛ፡- የነፃ ምርጫ መረጋገጥ ዋናው ዋስትናው ኢህአዴግ እነዚህን መስፈርቶች ተቀበልኩ ማለቱ ብቻ አይደለም:: ይህ መንግስት መጪውን ምርጫ «ካለፈው በተሻለ» ሁኔታ እንዲያዘጋጅ ከባዕዳን ተፅዕኖ እየተደረገበት መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው:: በእነሱ ግፊት ከተቃዋሚዎች ጋር ተደራድሬ ማሻሻያዎችን አደረግኩ ለማለት፣ ቢያንስ ቢያንስ ለባዕዳን ፍጆታ ሲል መሰረታዊ ያልሆኑ የማዘናጊያ ለውጦችን ሊቀበል ይችላል:: ግን ደግሞ ምን ያህል አሽብራቂ የሆኑ ማሻሻያዎች ቢያደርግስ እነኝህን በምን ተአምር ነው እኛ አስተማማኝ አድርገን በመቁጠር ሁኔታዎች ለነፃ ምርጫ ተመቻቹ ማለት የምንችለው? ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት አለኝ፣ መድብለ ፓርቲ ስርአት አስፍኛለሁ፣ ነፃ ፕሬስን የሚያረጋግጥ ህግ አለ፣ የኢትዮጵያውያን የመደራጀት መብት ተረጋግጧል ...ወዘተ ስላለ ብቻ ዛሬ አገራችን በዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት የምትተዳደር ዴሞክራሲያዊ አገር ነች ወይ? መልሱ ግልፅ ነው::

ይህ ደግሞ ወደ ሶስተኛው ነጥባችን ያመጣናል:: ለምሳሌ ባለፈው ምርጫ ኢህአዴግ አሸነፍኩ ያለው በያለበት በገፍ አጭበርብሮ ነው ብለናል:: ይህ ማለት ምን ማለት ነው? የመጀመሪያው መቼስ የምርጫ ህጉ አድሏዊ ነበር ማለት ነው:: ግን የወያኔ ማጭበርበር ዋና ገጽታ ይህ አልነበረም:: አጭበርብሯል የምንለው ከራሱ የምርጫ ህግ አንፃር እንኳን ቢሆን ፀረ ነፃ ምርጫ «ህገ ወጥ» ርምጃዎች ወስዶ አሸንፏል ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው:: እነዚህን አንድ ሺህ ገፅታ ያላቸው ማጭበርበሪያ ዘዴዎች የምናከሽፋቸው አዲስ አበባ ከነ አቶ መለስ ጋር ተደራድረን በምንፈራረማቸው ያሸበረቁ ሰነዶች አይደለም:: እነዚህን ለመቋቋም የምንችለው ምርጫው ካምፔይን ውስጥ ስንገባ፣ በየምርጫ ጣቢያው የሚፈፀሙትን ማጭበርበሮች፣ ሸፍጦች፣ አፈናዎችና ፀረ ነፃ ምርጫ ርምጃዎች ከስር ከስሩ እንደምንመዘግብና እንደምናጋልጥ፣ በእርግጥም በስፋታቸውና በተደጋጋሚነታቸው ይህን ምርጫ ከፉኛ የተጭበረበረ አድርገውታል የሚል ድምዳሜ ከደረስን ደግሞ በመጨረሻው ደቂቃ የድምፅ መስጠቱን ሂደት ቦይኮት እንደምናደርግ ከወዲሁ ለሚመለከተው ሁሉ በግልጽ ስናስቀምጥ ብቻ ነው:: ኢህአዴግ በድርድርና በልፈፋ ደረጃ ከሚሰጣቸው «ዋስትናዎች» ይልቅ የህዝባዊ ድላችን ማረጋገጫ አንዱ ይህ እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ በእጃችን ይዘን የምንቆየው «ማስፈራሪያ» ካርድ ይመስለናል::

### 4. በጋራ ፕሮግራም የጋራ ተወዳዳሪዎች ማሰማራት ይኖርብናል

የብቻ ሩጫ የትም እንደማያደርስ ዛሬ ሁሉም የተገነዘበው ያፈጠጠና የገጠጠ ሃቅ ይመስለናል:: ግን ይህንን ሃቅ መቀበልና ከዚህ መፍለቅ ያለበትን አማራጭ ስትራቴጂ መንደፍ የተለያዩ ነገሮች ናቸው:: እዚህም ላይ አሁን ያለው «በየምርጫ ጣቢያው አንድ ተቃዋሚ ብቻ እንዲወዳደር» የሚለው የህብረቱ አቋም ነው:: በጉዳዩ በህብረቱ ሰነድ የተጠቀመው ስትራቴጂ የሚከተለውን ይላል፡-

«ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ በሚካሄድበት ጊዜ ተቃዋሚ ድርጅቶች እንዲሳተፉ ህብረቱ የተቃዋሚ ድርጅቶችን ተወዳዳሪዎች የውድድር ሂደት ያስተባብራል፤ ይመራል:: በምርጫ ውድድሩ ወቅት በአንድ የምርጫ ጣቢያ አንድ የህብረቱ ተወዳዳሪ ብቻ እንዲወዳደር/እንድትወዳደር ያደርጋል::»

አሁን ባለው ሁኔታ በአንድ የምርጫ ጣቢያ አንድ የሕብረቱ ተወዳዳሪ ማለት ጨርሶ ትርጉም የሌለው ነገር ነው:: ሕብረቱ የድርጅቶች ሕብረት ነው:: የራሱ የሆኑ አባላት የሉትም:: የበጎ ራዕይ ሰነድ እንጂ አማራጭ የመንግስት ፕሮግራም የለውም:: ለውድድሩ የሚቀርቡት የአባል ድርጅቶች አባላት ናቸው:: እነዚህ ተወዳዳሪዎች ደግሞ ህዝብ ፊት ለምርጫ የሚቀርቡት የሕብረቱን የጋራ ራዕይ አንግበው ቢሆንም የየድርጅቶቻቸውን የፖለቲካ ፕሮግራም ይዘው ነው::

በዚህ ሁኔታ «በአንድ የምርጫ ጣቢያ አንድ የህብረቱ ተወዳዳሪ ብቻ» ሲባል ያለው አንድ ትርጉም አባል ድርጅቶችን አደራድሮና አግባብቶ በአንድ ምርጫ ጣቢያ የአንድ ድርጅት አባል ብቻ በተወዳዳሪነት የሚሰማራበትን ሁኔታ ያመቻቻል ማለት ብቻ ነው:: በቴሌ ኮንፈረንሱ ላይ እንደታየው አንዳንዶቹ የህብረቱ አባል ድርጅቶችም የህብረቱን አቋም የሚተረጉሙት በዚህ መልኩ እንደሆነ ዶክተር አድማሱ በግልፅ ሲያስቀምጡት ድርጅታቸው የሕብረቱን አቋም የተረዳው «አትሻሙ» በሚለው ትርጉሙ እንደሆነ ድርጅቶችም ጣቢያ «መሻማት» እንደሌለባቸው፤ ከዚህ በተረፈ ግን ሁሉም የፓርቲውን ፕሮራም አንግቦ የፓርቲውን አላማ ለህዝብ ለማስተዋወቅ ካምፔይን ማድረግ እንደሚችል ጠቁመዋል:: ይህ አንድ አባል ድርጅት በዚህ አካባቢ የማሸነፍ እድል ካለው ሌላ አባል ድርጅት እጩውን በዚያ አካባቢ አያሰማራ የሚለው የህብረቱ የ«አትደራረሱ» ስትራቴጂ ጨርሶ የማያዋጣ አካሄድ ነው:: ለምን?

አንደኛ፡- ለምሳሌ አባል ድርጅቶች ለሃገራችን ወሳኝ በሆነው የመሬት ጥያቄ ሁሉም ተመሳሳይ አቋም የላቸውም:: የአንዳንዶቹ ፕሮግራም መሬት የግል ሃብት እንዲሆንና መሸጥ መለወጥ እንዲቻል የሚሟገት ፕሮግም ነው:: የሌሎች ደግሞ ይህንን አካሄድ ይቃወማል:: በመሬት ፖሊሲ ጉዳይ ድርጅቶች የተለያዩ አቋሞች እንዳላቸው እየታወቀ በዚህ ጥያቄ ላይ በቅድሚያ አንድ (የኮምፕሮማይዝ) የጋራ አቋም (ማለትም አንድ የጋራ ሽግግር መንግስት የፖለቲካ ፕሮግራም) ሳይነደፍ የግል ሃብት የሚለው ድርጅት ደጋፊዎቹን በዚህ ጥያቄ የተለየ አቋም ለሚያራድ ድርጅት ድምፅ እንዲሰጡ ከጠራ የህብረቱ አባል ድርጅቶች ወይ የየራሳቸውን ፕሮግራም ወይም አንዱ የሌላውን አቋም ወይ ደግሞ ጭራሹን ደጋፊዎቻቸውንና ከእነሱም አልፎ መራጩን ህዝብ «ሲርየስሊ» እንዳልወሰዱዋቸው የሚያሳይ አስገራሚ አካሄድ ይሆናል::

ሁለተኛ፡- ምንም እንኳን በዚህም ቁልፍ ጥያቄ ላይ የህብረቱ አቋም ገና ግልጽ ባይሆንም «ካሸነፍን ወያኔን አስወግደን የጋራ ሽግግር መንግስት እናቋቁማለን» የሚል ስትራቴጂ አለን:: በዚህ መልክ ተወዳድረን ከዚህ ምርጫ ስብጥርጥርና ተቃራኒ አቋሞች ያላቸው ተቃዋሚዎች በራሳቸው ፕሮግራምና ደጋፊዎች ብርታት ብቻ ሳይሆን የተለየ ፕሮራግራም በሚያራምዱ ሃይሎችም ድጋፍ «በአሸናፊነት» ቢወጡ የሚቋቋመው መንግስት የትኛውን ፖሊሲ ይከተላል?

በአንድ ምርጫ ጣቢያ አንድ የታቃዋሚዎች ተወዳደሪ ከሚለው አቋም ይልቅ ትግሉ «በእኛና በእነሱ» መሃከል እንዲሆን በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች፣ የሃገራችን ዴሞክራቶች በሙሉ የእኛ የሚሉት አንድ የጋራ ተወዳዳሪ ይኑር ብሎ በግልጽ ማስቀመጥ ላለንበት ሁኔታ ይበልጥ ተስማሚ ስታራቴጂ ይመስለናል:: ይህን በአንድ የምርጫ ጣቢያ አንድ ሁላችንም የእኛ የምንለው አንድ የህብረቱ የጋራ ተወዳዳሪ የሚል ስታራቴጂ ለመቀበል መጀመሪያውኑ በሁለት ጥያቄዎች ላይ ግልጽ መሆንና በዚህ በኩል ጥራት ከተገኘ አንድ መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታ ማሟላት ይኖርብናል::

ግልፅ መሆን ካለባቸው ጥያቄዎች የመጀመሪያው በዚህ ምርጫ ተሳትፈንና በድል አድራጊነት ወጥተን ወያኔን የሚተካ መንግስት እናቋቁማለን ስንል ይህ የምናቋቁመው መንግስት ምን አይነት መንግስት ይሆናል? የሚለው ጥያቄ ነው:: የምናቋቁመው ጊዜያዊ የዴሞክራሲ ሽግግር መንግስት እንደሆነ ሰፊ ስምምነት አለ:: ይህ የጋራ የሽግግር መንግስት ወሳኝ በሆነ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ ማሕበራዊና ዲፕሎማሲዊ ጥያቄዎች ምንም አይነት ዘላቂነት ያላቸው ውሳኔዎች የመውሰድ ስልጣን የሌለው፤ እስከተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ➔

ምርጫ ድረስ የሃገሪቱ አስተዳደር «አደራ» የሚባል «ኬርቴከር ገቨርንሜንት» መልክ ይኖረዋል የሚለውም አስተሳሰብ ተቀባይነት ያለው ይመስለናል። እንዲህ አይነቱ አካሄድ ካለፈው ባገኘነው ትምህርትና ዛሬ ባለው የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ትንተና የሚታገዝ ትክክለኛ አካሄድ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ባለፉት ሰላሳ አመታት ከንጉስ ወደ ደርግ፣ ከደርግ ጊዜያዊ መንግስት ወደ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ፤ ከዚያ ወደወያኔ የሽግግር መንግስትና ወደ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እየተባለ በተፈራረቁበት የሽግግር ተብዬ ሂደቶች ብዙ የተንከራተተ ህዝብ ነው። እነዚህ የሽግግር ወቅቶች ፀረ ህዝቦች ብቻ ከጊዜያዊነት ወደ ቋሚ መንግስትነት እንጂ ህብረተሰባችንን በሙሉ ከፀረ ዴሞክራሲ ስርአት ወደ ዴሞክራሲ ስርአት ሳያሸጋግሩ ያለፉና የጥፋት ሂደቶች ነበሩ።

ከዚህ ተገቢውን ትምህርት ከቀሰምን ከመጪው ምርጫ ሂደት የምንጠብቀው ዋና ቁም ነገር በተጨናገፈውና በከሸፈው በኢህአዴግ የሽግግር ሂደት መቃብር ላይ አገራችንና ህዝባችን ወደ ሰላምና ዴሞክራሲ በተረጋጋ ሁኔታ የሚሸጋገሩበት ሌላ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ወቅት እንዲከፈት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው።

የመጪው ምርጫ ታሪካዊ ተልእኮ ይህ በመሆኑ ድርጅቶች ወገናዊ ፕሮግማቸውን ይዘው ለህዝብ ምርጫ ለመቅረብ ከሽግግሩ ወቅት ባሻገር ብቻ የሚመጣውን ቀጣዩን ምርጫ መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ህዝባችን በተሳካ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ዘመን አማካኝነት የተሰበጣጠሩ ድርጅቶች ከሚያቀርቧቸው አማራጮች መሃል ይሆነኛል የሚለውን ለመምረጥ የሚችልበት ደረጃ እስኪደርስ ድረስና እንዲያውም እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ዛሬ በኢህአዴግ ስታሊናዊ ህገ መንግስት የተነሳ መርጠም ምንም ለውጥ ለማያመጣበት ምርጫ አማራጮችን ማንጋጋት ምንም ፋይዳ አይኖረውም።

በዚህ ግልፅ ከሆንንና ከተስማማን ሌላ መብራራት የሚኖርበት ነጥብ «ድርጅታዊ ነፃነት»ን የሚመለከተው ነጥብ ነው። የጋራ ተወዳዳሪዎች የሚለውን ሃሳብ ለጊዜውም ቢሆን በጥርጣሬ አይን የሚያዩ ወገኖቻችን የሚያነሱት ይህ ክርክር እስከዚህም አስቸጋሪ ነጥብ ሆኖ አናገኘውም። ረጋ ብለን ካየነው ጊዜያዊና የተወሰነ ታሪካዊ ተልዕኮ ባለው ህብረት ውስጥ መሰባሰባችን ድርጅታዊ ነፃነታችንን አልነካውም። ህብረቱ ውስጥ የገባነው ስማችንን፣ መዋቅራችንን፣ የፖለቲካ ፕሮግራማችንን፣ የወደፊት እድላችንን እንደያዝን ነው። ምርጫው ውስጥ ስንወዳደርም ድርጅታዊ ማንነታችንን ሸሽገን አይደለም። ለአንዲት የምርጫ ወቅት፣ ለተወሰነ ታሪካዊ ተልእኮ ሁላችንም በጋራ በተስማማንበት ጊዜያዊ የሽግግር መንግስት ፕሮግራም አማካኝነት ድርጅታችንን ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የሃገራችንን ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ወክለን የምንወዳደር እንደሆነና በቀጣዩ ምርጫ ግን ወገናዊ አማራጮቻችንን ይዘን እንደምንቀርብ ከወዲሁ ለህዝባችን ግልፅ አድርገን የምንገባበት ሂደት ነው።

ነገሩ እንዲህ ግልጽ ሆኖ ሳለ «በድርጅታዊ ነፃነት» ሰበብ ሁሉም በየበኩሉ በመሰለው ይሂድ ማለት እንዳለፈው ምርጫ ሁሉም ድርጅት «የቻለውንና የበኩሉ» በወያኔ ፓርላማ ውስጥ ወንበር ለማግኘት ይራኮት ማለት ይሆናል። ይህ አካሄድ ደግሞ አንዱ «ከሁሉ ጎልቶ የሚታይ ተቃዋሚ ሆኖ ለመቅረብ» የሚሞከርበት አካሄድ ስለሚሆን የመጨረሻ መጨረሻ የምንወዳደረው ከወያኔ ጋር ሳይሆን እርስ በርስ የሚሆንበት አደገኛ ሁኔታ እንደሚፈጠር ቢያንስ ለኛ ግልጽ ነው። በዚህ ሁኔታ መጪውንም፣ ቀጣዩንም፣ የወዲያኛውንም ምርጫ የማሸነፍ ምንም ዕድል አይኖርም።

ያለውን መንግስት በምርጫ አሸንፈን ሌላ መንግስት እናቋቁማለን፣ ለዚህም በያለበት የጋራ ተወዳዳሪ እናቀርባለን ብለን ከተነሳን ደግሞ ይህንን ለማድረግ ማሟላት ያለብን ግልፅ ቅድመ ሁኔታ አለ። የጋራ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር መንግስት አማራጭ ፕሮግራም ያስፈልገናል። ምርጫው እየተቃረበ ባለበትበአሁኑ ወቅት ህብረቱ ከበጎ ራዕይ ካታሎግ የዘለቀ የፖለቲካ ፕሮግራም አለው ለማለት የምንችልበት ደረጃ ላይ አይደለንም።

እርግጥ መለስተኛ የፖለቲካ ፕሮግራም ተብሎ የተሰራጨ ሰነድ አለ። ነገር ግን ነፃ ምርጫ፣ የህግ የበላይነት፣ ነፃ ፕሬስ፣ የገበያ ኢኮኖሚ፣ የህዝቦች እኩልነትና አንድነት ወዘተ የሚሉ ወያኔ/ኢህአዴግም ቢሆን ቆሜላቸዋለሁ የሚላቸውንና ከፖለቲካ ፕሮግራምነት ይልቅ ወደ በጎ ራዕይነት የሚያዘነብሉ መፈክሮችን ይዘን መጪው ምርጫ ካምፔይን ውስጥ መሳተፍ አንችልም። እንዲያውም እስካሁን የተሞከሩት ህብረትና የጋራ ትግል ሙከራዎች አንዱ ድክመት በራዕይ ደረጃ የተንሳፈፉ አላማዎችን ብቻ አንግቦ መጓዝ ላይ ማተኮራቸው በመሆኑ ከዚህ አልፈን የጋራ የሽግግር መንግስት ፕሮግራም የሚነደፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርብናል። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ አላማችን «ይህንን መንግስት አስወግዶ በሌላ ዴሞክራሲያዊ መንግስት መተካት» ተብሎ በግልፅ በተቀመጠበት ሁኔታ ለዚህ ጥያቄ ትኩረት አለመስጠት በጣም ግራ የሚያጋባ አካሄድ ይሆናል። መንግስትን በመንግስት ለመተካት የሚቃጣ ሃይል አማራጭ የመንግስት ፕሮግራም ይዞ መንቀሳቀሱ መሰረታዊ የሆነ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ለማንም ሊሰወር የሚችል ሎጂክ አይደለም።

*5 በተጨባጭ መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች*

ከፍ ብለው በተጠቀሱት ወሳኝ ጥያቄዎች ህብረቱ ባስቸኳይ ተወያይቶ ስለመጪው ትግል ግልፅ የሆነ አቅጣጫ ከያዘና አባል ድርጅቶች በሙሉ ልብ ለአንድ ግልፅ አላማ ታግለው የሚያታግሉበት ሁኔታ ካልተመቻቸ «ያለውን መንግስት በነፃ ምርጫ ተፋልሞ ለማሸነፍ» በሚል ድፍን መፈክር ብቻ ህብረቱ እንዴትና ለምን ሊቀጥል እንደሚችል አይገባንም። በደፈናውና በራዕይ ደረጃ የተቀመጡ አላማዎችና ጥራት የሌላቸው ስትራቴጂዎች አሁንም እጅ ተወርች አስረው ከፊታችን የተደቀኑትን ተጨባጭ ተግባራት እንዳናይ አድርገውናል። ከእነዚህ ተግባራት አንዱና የመጀመሪያው ካለንበት ውዥንብር ሰፊ ውይይት አካሂደን መውጣትና ጥራት ያለውና ለትግል የሚያመች አቋም ለሃገራችን ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ማስጨበጥ መሆን አለበት። እዚህ ደረጃ ከደረስን የሚቀጥለው ዕርምጃ ምን መሆን እንዳለበት መኢሶን እንደሚከተለው ሃሳቡን ያቀርባል:-

*1ኛ/ የዴሞክራታይዜሽንና የነፃ ምርጫ ኮሚሽን ማቋቋም*

ይህ ኮሚሽን የነፃና ፍትሃዊ ምርጫ መስፈርቶችን አስመልክቶ መሰረታዊ በሆኑት ጥያቄዎች ከመንግስት ጋር የሚካሄዱትን ድርድሮች በሃላፊት ያካሂዳል።

በእነዚህ ለመንግስት የሚቀርቡ መሰረታዊ ነጥቦችና በአጠቃላይ በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ጉዳይ ሕዝቡ ግንዛቤዎች እንዲያገኝ፤ ተወዳዳሪዎችና በምርጫው ወቅት በየምርጫ ጣቢያው የተወዳዳሪዎች እማኞች ሆነው ሂደቱን የሚቆጣጠሩ ዜጎች መብት፣ ሃላፊነትና ተግባራት ግንዛቤ ለማስጨበጥ ስብሰባዎች ያዘጋጃል፤ ፅሁፎች ያወጣል።

በእነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ በዲፕሎማሲው መስክ የሚካሄዱትን እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፤ በምርጫው ካምፔይን ወቅት በያለበት የሚፈፀሙትን ፀረ ነፃ ምርጫ ድርጊቶች በተቀነባበረ መልክ ይሰበስባል፤ ይፋ ያደርጋል፤ እንዲታረሙ ሕጋዊና ፖለቲካዊ ርምጃዎች ይወስዳል።

በምርጫው ማብቂያ ላይ አጠቃላይ የምርጫውን ሂደት የሚገመግምና ለኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ለአለም አቀፍ ኮሚኒቲው የሚቀርበውን ሪፖርት ረቂቅ ያዘጋጃል።

በዚህ ግምገማ በመመርኮዝ ተቃዋሚዎች በድምፅ መስጠቱ ሂደት ይሳተፉ ወይስ ባይኮትያድርጉ በሚለው ጥያቄ የውሳኔ ፕሮፖዛል ያቀርባል ወዘተ።

*2ኛ/ የሽግግር መንግስት አማራጭ ፕሮግራም አርቃቂ ኮሚቴ*

ይህ ፕሮግራም በሃገራችን ዴሞክራሲን ለማስፈን ለሚያስፈልገን የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ወቅት የምንገለገልበት፣ በሚቀጥለው የ2002 ዓ.ም ምርጫ ሁሉም ድርጅቶች የየራሳቸውን ፕሮግራም ይዘው በሕዝብ ፊት መቅረብ እስኪችሉ ድረስ መንግስት ይዘን በተግባር የምናወለው ጊዜያዊ የኮምፐርማይዝ ፕሮግራም ነው።

በምርጫው በገፍ አጭበርብሮም ሆነ በሃቅ ተወዳድሮ ኢሕአዴግ በአሸናፊነት ከወጣ ሃገራችን ይህ መንግስት ተሸንፎ ሃቀኛ የሆነ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ፈር እስኪትይዝ ድረስ ሕዝብ የመቀስቀሻና የማደራጃ መድረክ ሆኖ ይቀጥላል።

ፕሮግራም አርቃቂው ኮሚቴ በየድርጅቶች የተሰየሙ አባላትና በእነሱ በተጠቆሙ ከሲቪል ሶሳይቲው ከታወቁና በየመስካቸው እውቀትና ልምድ ካካበቱ ግለሰቦች፣ ምሁራንና ፕሮፌሽናሎች የተውጣጣ ይሆናል።

ፕሮግራሙን ለማርቀቅ መነሻ አድርጎ የሚነሳው የአባል ድርጅቶችን የፖለቲካ ፕሮግራም ቢሆንም ቅሉ ከነሱ ውጭ ያሉ የሰራተኞችና የገበሬዎች፣ የአሰሪዎች፣ የነጋዴዎችና ኢንቨስተሮች፣ የጋዜጠኞች፣ የመምሕራን፣ የልዩ ልዩ ባለሙያዎች (ኢኮኖሚስቶች፣ የአካባቢ ጥበቃ ኤክስፐርቶችና ሃኪሞች፣ በውጭ ያሉ ምሁራንና ባለሙያዎችን ወዘተ) የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የሃይማኖት አባቶች ስብስቦችና ተጠሪዎችንም በማነጋገር ለአባል ድርጅቶች ረቂቅ ፕሮግራም የማቅረብ ማንዴት ይኖረዋል።

በዚህ መልክ ሰፊ ውይይትና ምክክር ተደርጎበት የሚረቀው ፕሮግራም የሕብረቱ አባል ድርጅቶች ተወያየተውበት ካፀደቁት በኋላ አርቃቂ ኮሚቴው የፕሮግራሙን መሰረታዊ ነጥቦችና አማራጮች በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ መደረግ ስላለበት ቅስቀሳና እንቅስቃሴ ስትራቴጂ አውጥቶ ተግባራዊነቱን ይከታተላል ➔

ወዘተ...።

*3ኛ/ የጋራ ተወዳዳሪዎች ስያሜና አሰራ ኮሚቴ*

እንደላይኛው ይህም ኮሚቴ በአባል ድርጅቶች በተጠቆሙ አባላት፣ ከአባል ድርጅቶች አባልነት ያልተመዘበም ቢሆኑ በጎ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ ከሚባሉ የሲቪል ሶሳይቲው አባላት፣ ከታዋቂ ዴሞክራቶች፣ ከሃገር ሽማግሌች፣ ከምሁራን የተውጣጣ ይሆናል።

ተወዳዳሪዎችን ለመምረጥና ለማስማራት በመጀመሪያ የሚጠቀምበት መስፈርት የድርጅት አባልነት ቢሆንም፤ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ከተደራጁ ሃይሎች ብቻ በማውጣጣት የምርጫ ጣቢያዎችን በሙሉ ለመሸፈን አስቸጋሪ ስለሚሆንና ከዚህም በላይ ደግሞ በሙያቸውም ሆነ በሕዝብ ዘንድ ባላቸው ቀበሌታና ከበሬታ ተወዳድረው በማሸነፍም ሆነ በአጠቃላይ በትግሉ ሊያደርጉ የሚችሉት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ሆኖ ከተገመተ የጋራ ፕሮግራሙን የተቀበሉ በድርጅት ያልታቀፉ ዴሞክራትና አገር ወዳድ ግለሰቦችንም ለተወዳደሪነት የመጠቆም ሃላፊነት ይኖረዋል።

በዚህ መልክ የተመለመሉት ተወዳዳሪዎች ለውድድር ለመመዝገብ በሚያደረጉት ጥረት ከምርጫ ቦርዱ አንፃር ማሟላት የሚኖርባቸውን ፎርማሊቲዎች በትክክል እንዲያሟሉ ምክርና እገዛ ይሰጣል፤ መዝጋቢው ባለስልጣን ሊፈጥር የሚችላቸውን መሰናክሎች ለማስወገድ ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው የዴሞክራታይዜሽንና የነፃ ምርጫ ኮሚሽን ጋር በመተባበር ይሰራል ወዘተ...።

*4ኛ/ ሌሎች ኮሚቴዎችን ስለማቋቋም*

ትግላችን የሰመረ እንዲሆን ከፍ ብለው ከተጠቀሱት ኮሚቴዎች በተጨማሪ በሂደት ሌሎችም ኮሚቴዎች መመስረት እንዳለባቸው ግልፅ ነው። ከእነዚህ ውስጥ ለምሳሌ የገንዘብ ሰብሳቢ ኮሚቴ ቁልፍ ሚና ከሚጠበቅባቸው ግብረ ሃይሎች አንዱ ነው። ከፍ ብለን የጠቀስናቸውን ተግባራት በስራ ለመተርጎም ከፈለግን በሺህ ሳይሆን በመቶሺህ እንዲያውም ከዚያ በላይ የሚተመን የፋይናንስ አቅም ያስፈልገናል። ነገር ግን እንዲህ አይነት ሰፊ ድጋፍ ለመሰብሰብ ግልፅ የሆነና ድጋፍ የሚጠየቁት ወገኖች የሚያምኑበት አቅጣጫ መነደፍ ይኖርበታል። ይህ ከመደረጉ በፊት የድጋፍ ገንዘብ ለመሰብሰብ የሚደረገው ጥረት ምንም የሚያረካ አይሆንም የሚል እምነት አለን።■

*የመላ ኢትዮጵያ የሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)*

*መጋቢት 1996 ዓ.ም*

# "እነ ዶ/ር ገብረሕብ...

(ከገፅ 25 የዞረ)

ነገር እየተደረገ ነው። ታዲያ ሁለቱም ነገሮች ዓለም አቀፍ ሕግን የሚፃረሩ ናቸው። በዚህ በኩል ማሳመን የሚቻል ነገር የለም። አሁን ነገሩን ቢያገላብጡት የሚለወጥ ነገር የለም። የፈለገ ነገር ቢባል እና ቢደረግም ፖሊስ ከመከላከያ ሠራዊቱ ጋር በመሆን የፈፀመውን ግድያ ማስተባበል ወይም መካድ የሚቻል አይደለም። ከእንግዲህም የአኙዋኮች መገደልና የመንግስት መከላከያ ኃይል ጉዳይ መታየት የሚኖርበት በዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ነው።

ኢትኦጵ፡- ነፃ የሆነ አጣሪ ኮሚሽን መቋቋም አለበት የሚባለውስ?

አቶ ኦኬሎ፡- እሱ አይደለም ከአሁን ወዲያ ችግሩን ማየት ያለበት፤ አለም አቀፉ ማሕበረሰብ ነው። ሁኔታው ወደዚያ ደረጃ ያደገ ነው። ስለ ጋምቤላ ጉዳይ፣ ስለአኙዋኮች ጉዳይ መቅረብ አለበት የሚባል ሪፖርት ካለ ያ ሪፖርት መቅረብ የሚኖርበት ለዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ነው። ከዛ ቀጥሎ ውይይት ያው የጋራ በመሆኑ የተበደሉት አኙዋኮች የማይወያዩበት ምክንያት ሊኖር አይችልም። በመቀጠል እንዴት ነው የኢኮኖሚው፣ የፖለቲካው፣ የደህንነቱ ዋስትና የሚለው ይታያል። ከዚህ በተረፈ አሁን ተቋቋመ የሚባለውና በጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንቱ በአቶ ከማል በድሪና በምርጫ ቦርዱ ሰው የሚመራው «አጣሪ» የሚባለው ኮሚሽን ውጤት አያመጣም።

እነሱ በነበሩበትና በሚመለከቱት ሁኔታ ነው በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ችግር ያለው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የጠማው ፍትህና ትክክለኛ ዲሞክራሲ ነበር! ነገር ግን ይህ ጥማት እርካታ እንዲያገኝ የድርሻቸውን ይወጣሉ ተብለው የተጠበቁ ሰዎች ሃላፊነታቸውን አልተወጡም። ለጋምቤላ ግድያ ብቻ ሳይሆን በተቀሩትም የኢትዮጵያ ክልሎች ችግር የፈጠረው ነገር የዴሞክራሲ መታመቅ ነው። ዲሞክራሲው «አለ» ይባላል። ነገር ግን የለም። አሁንም የእነ ከማል በድሪ በኮሚሽኑ ውስጥ መኖር የመረጃዎችን ደብዛ ለማጥፋት ካልሆነ በቀር ከዚህ በፊት እንዳየነው ውጤት የሚፈለገውን አያመጣም። ከማል በድሪ ነፃ ሰው ቢሆኑ ኖሮ እንደ ምርጫ ቦርድ ሊቀመንበርነታቸው በኢትዮጵያ ነፃ ምርጫ በኖረ ነበር።

ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ይጠቅማል፣ የጋምቤላውን ረብሻ ምክንያት ያስረዳል የሚባለው ሪፖርት ቢቀርብላቸው ያቃጥሉታል እንጂ ምንም አያደርጉትም። አሁን የሞቱት ሰዎች ቁጥር እንኳን እኔ እስከሄድኩ ድረስ ከ400 በላይ ነው የደረሰው። ከዚያ በኋላ ደግሞ እንደገና የተካሄደው ውጊያ በሄሊኮፕተር ነበር የታጀበው። ሌላም አካባቢ እንደዚሁ ነበር፤ ገበሬዎችን መሳሪያ እናስወጣለን እያሉ ሲያሰቃዩአቸው ብዙ ሰው ሞቷል። እስካሁን ድረስ በአጠቃላይ ሞተዋል ተብሎ የሚገመተው ከ1000 በላይ ይደርሳል። ይህን ግን የኢትዮጵያ መንግስት እየተቀበለው አይደለም። ይሄ ቀልድ ነው፣ ጨዋታ ነው እያለ ይገኛል። ስለዚህ ይህ አስፈላጊ አይደለም።

ኢትኦጵ፡- አቶ ኦኬሎ በእውነት እዚያ ቦታ ላይ የነበሩ ወሳኝ ሰው ነበሩ፤ ምናልባትም ሲሰማ የሚችል ካለ ይህ ለዚያ አካባቢ ችግር መፍትሄ ይሆናል ብለን ነው የምናስበው፤ አንድ ነገር ግልፅ እንዲሆንልን እዚያ አካባቢ (ጋምቤላ) ሰራዊቱ መቼ ነው የገባው?

<u>አቶ ኦኬሎ</u>፡- ሠራዊቱ እኔ እያለሁም ገብቷል። በሻለቃ ደረጃ ነው፤ ሻለቃ ፀጋዬ ነበር የሚመራው፤ መቀመጫውም እዚያው ጋምቤላ ነበር ክልሉ። ያው ከእኛ ጋር አንዳንድ ነገር እየተነጋገርን ነበር የምንሰራው። እሱምኮ እያየ ነው የሰዉን መሞት፤ እሱ ደግሞ ከእኔ በፊት በነበረው ችግር ምክንያት እዚያው ቆይቷል።

ኢትኦጵ፡- እርስዎ አገር ለቀው ከወጡ በኋላ በቤተሰብዎ ላይ የደረሰ ተፅዕኖ አለ?

<u>አቶ ኦኬሎ</u>፡- እኔ እንደሄድኩ ባለቤቴ ታስራለች፤ መከላከያ ግቢ ውስጥ ነው የታሰረችው። እንደገና ከእሷ ምን ይገኛል ብለው ነው የፈቷት። አንድ ወንድሜን ደግሞ ክፉኛ ደብድበውት ደም እስከመትፋት ደርሶ ነበር፤ እሱንም በመጨረሻ ለቀውታል።

ኢትኦጵ፡- ባለቤትዎ አሁን ከእርስዎ ጋር ናቸው?

<u>አቶ ኦኬሎ</u>፡- አልወጣችም፤ እስካሁን እዚያው ነች። ምናልባት ከአሁን ወዲያ ልትመጣ ትችላለች! ለነገሩ እርጉዝ ስለነበረች ነው መንቀሳቀስ ያልቻለችው። አሁን ግን መውሰድ ይቻላል።

ኢትኦጵ፡- በጋምቤላ አካባቢ ነዳጅ ስለተገኘ ነው ይህ ሁሉ ችግር የመጣው፤ የሚባለውን እርስዎ እንዴት ያዩታል?

<u>አቶ ኦኬሎ</u>፡- ደህና... ይሄ ነዳጅ የተገኘው አሁን አይደለም፤ ጋምቤላ ውስጥ ነዳጅ አለ የተባለው በ1973 ዓ.ም ነው። ያን ጊዜ ነው። ሆኖም ይህን ያህል ችግር አልመጣም። ነዳጁን በሚመለከት ችግሮች ቢኖሩም ሰው ገድለህ አይደለም ወደ ነዳጅ የምትሄደው። ነዳጅ መኖሩ ከታወቀ ከ1973 ዓ.ም በኋላ ታንከሮች እዚያው ከተማ ውስጥ ተሰርተዋል። ለሪዘርቬሽን ማለት ነው። አኙዋኮች ለነዳጅ ሲሉ ሌላውን ሕዝብ ይውጣ አላሉም። ይልቁንም የኢሕአዴግ መንግስት ራሱ ሰዎቹ እንዲኖሩ አይፈልግም። አሁን እንደውም ቀጥታ መንገዱን ይዟል።

ነዳጅ ወዳለበት ቦታ እየገባ ነው፣ እየተጋጨ ነው፤ ሁል ጊዜ ያቺን መንገድ ከፍቶ ነዳጅ ወዳለበት ለመግባት። ነዳጅ ስለተገኘ አኙዋክ መገደል አለበት የሚል ሕግ የለም። ነዳጅ ስለተገኘም ጋምቤላ ከኢትዮጵያ መንግስት ውጭ መሆን አለባት የሚል አቋምም የለም፤ አልነበረም። ምክንያቱም ከ1973 ጀምሮ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ነዳጅ መኖሩ ከታወቀ ጀምሮ ይህ ሁኔታ አልነበረም። ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ብዙ መረጃዎች አሉ። እየተጠና ነው፤ በተለይ የአሁኑ መንግስት ምን ይሰራ እንደነበረ፤ እንዳውም እዚያ ያሉ አኙዋኮች ከዚያ ወጥተው ይጓዙና ሱዳን ሲደርሱ እንኳ ሊያጠፋቸው ነው የሚያስበው። ነዳጁ አካባቢ ሰው እንዳይደርስ ነው የመንግስት አላማ። ባለው ስምምነት ላይ እንዴት ይሰራ እንደነበረ ጥናቶች ያመለክታሉ። እና ይህ ትክክል አይደለም፤ መንግስት ራሱ ነው ስህተት ውስጥ የገባው።■

# ክቡር...

(ከገፅ 31 የዞረ)

ቴዎድሮስ፡- በማህበራዊ ግንኙነት መድረክ ከምንቀሳቀስባቸው ነገሮች አንዱ የተቸገሩ...የታመሙ...ለህክምና የሚሆን ገንዘብ ያጡትን ለመርዳት የሚቻልበት የሶሻል ኮሚቴ ተቋቁሟል፤ በዚህ ኮሚቴ ውስጥ በስፋት እሳተፋለሁ። ይህ ከበጎ ሃሳብ የሚመነጭ ነው።

በሌላም በኩል የኢትዮጵያ አርቲስቶች የበጎ አድራጎት ህብረት በሚል ከተከበሩና ከአንጋፋዎቹ አርቲስቶች ጋር ባቋቋምነው ማህበር የወደቁና የተረሱ...ህክምና የማያገኙ... ጡረታ ወጥተው መንቀሳቀሻ ያጡትን ታላላቅ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችን እየረዳንና እያስታወስን ነው።...ይህም የምኮራበት የመልካም አርአያ ተግባር ነው።... በመሆኑም ከቤተሰቤ... ከጓደኞቼ... ከስራ ባልደረቦቼ ጋር ጤናማ ግንኙነት አለኝ።

ኢትኦጵ፡- ከቀለማት ሁሉ ያንተ ምርጫ የትኛው ነው?

ቴዎድሮስ፡- ፐርፐል (ሃምራዊ) ደስ ይለኛል።

ኢትኦጵ፡- ቴዲ የሚመርጠው የምግብ አይነት?

ቴዎድሮስ፡- ከምግብ ክትፎና ሃምበርገር ይመቹኛል።

ኢትኦጵ፡- ታዲያ ምነው ሠውነትህ ቀጠን አለ?

ቴዎድሮስ፡- አንተ ሰውዬ ለቀቅ አርገኝ።... መቼም ጤና የተሞላበት ሠውነት እንዳለኝ አምናለሁ።...ስለበላህ ብቻ ትወፍራለህ ማለትም አይቻልም።

ኢትኦጵ፡- የመጠጡስ ነገር እንዴት ነው?

ቴዎድሮስ፡- በፍፁም አልጠጣም።

ኢትኦጵ፡- የረሳሁት ነገር!... የማርሻል አርት ባለሙያ ነህ አይደል?

ቴዎድሮስ፡- በሚገባ እንጂ።

ኢትኦጵ፡- ለዚህ ነዋ ከመጠጡ የሸሸኸው?

ቴዎድሮስ፡- አንድም በዚህ ነው...የማርሻል አርት መመሪያ መጠጥን አይፈቅድም።...ያም ባይሆን ግን እኔ ከቀድሞውም ቢሆን መጠጥ!... ጫት!... ሲጋራ ከማይጠቀሙ ባለሙያዎች ተርታ ነው የምሰለፈው።

ኢትኦጵ፡- መቼም ሠው የወደፊቱን ይተልማልና →